# *የሚኒሶታ ኢትዮጵያውያን የወያኔን የከፍፍል ሴራ እናክሽፍ።*

## *በወያኔና በአላሙዲ  የሚደገፈውን በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ስፖርት ፌዴሬሽን አንድን (ESFNA ONE)እንቃወም*

ዘረኛውና ጠበቡ የወያኔ ማፊያ ቡድን በመንግስት ስም በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ከተፈናጠጠበት ወቅት ጀምሮ በአገሪቱና በሕዝብ ላይ ዘርፈ ብዙ በደል ፈጽሟል። ሕዝብ አብሮ እንዳይቆም፣ እንዳይመክር፣ እንዳይቃወመው ፣ በጋራ ሆኖ መብቱን እንዳያስከብር ለማድረግ በአገሪቱ የሚገኙትን የዲሞክራሲ መሰረት የሆኑትን  የሙያና የሲቪክ ማህበራትን ተላጣፊ ማህበራትን በማቋቋምና በጉልበት ከፋፍሏል፤አፍርሷል። እንቅስቃሴያቸውንም ገድቦ ምርኮኛ አድርጓቸዋል።በሥልጣን ላይ የሚገኘውም በጠመንጃ ኃይል ነው። የከፍፍል መረቡንም በማርዘም በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵውያን መሰበሰቢያ ቦታዎችን የሃይማኖት፣ የማህበረሰብ፣ የስፖርት ተቋማትን ለመከፋፈልና በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ በፈረንጆች አቆጣጠር ከ2008 ( በኢ.አ ከ2000ዓ.ም) ጀምሮ እቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለዚህም ማስረጃው በተለያዩ ቦታዎች በሃይማኖትና በማህበረሰብ አከባቢዎች እያደረገ ያለው የከፍፍል ድርጊትና እንቅስቃሴው  ነው።

በ1984 ( በ1976ዓ.ም) በጥቂት ኢትዮጵያዊያን ተቋቁሞ ዛሬ በሰሜን አሜሪካ ትልቅ የኢትዮጵያውያን የስፖርትና የባሕል መገለጫ የሆነው ድርጅት የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ( Ethiopian Sports Federation in North America = ESFNA)የወያኔዎችና የቱጃሩ የወያኔ ተላላኪ የሼክ አላሙዲ የጥቃት ሰለበ እንዲሆን ተወስኖ የድርጅቱን ስም በቅጥያነት በመጠቀም  ESFNA ONE እያሉ ክፍፍል በመፈጸም ላይ ይገኛሉ።  ለኢትዮጵያውያን የሚያስቡ በመምሰል እኛ የምንሰራው ስፖርት ነው በማለት እያታለሉ ሕዝቡን ይካፋፍላሉ። ወጣቶችን  ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተዘረፈው ገንዘብ ነፃ ትራንስፖርትና ሆቴል አገልግሎት  ፣ የኪስ ገንዘብ እንሰጣለን በማለት ያባብላሉ። ዋናው የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን ዓመታዊ ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት ተመሳሳይ ዝግጅት በማድረግ የከፍፍል ተልእኳቸውን በማወጣት ላይ ናቸው። በፈራንጆች  አቆጣጠር በ2012 እና 2013 በዋሽንግተን ዲሲ ትልቅ ስታድየም(RFK stadium) ተከራይተው  ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ተቃውሞ ባዶ ስታድየሙን ይዘው ቀርተዋል።

አሁን በ2014 ( 2006ዓም) በሚኒሶታ የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን የሰሜን አሜሪካ ዝግጅት (ESFNA ONE) እናደርጋለን በማለት የወያኔ ቡድን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነው ። በሬድዮ መግለጫ እየሰጠ ነው። በድብቅ ሥራውን እየሰራ ነው።ሚኒሶታ ተደፍረናል። የወያኔዎችን የከፍፍል ሴራ ማክሽፍ ይጠብቅብናል።  የሚከተሉትን እርምጃዎች እንድትወስዱ እናሳስባለን፡-

1. *የዘንድሮው የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ ያዘጋጀው ዝግጅት የሚደረገው Bay Area, Sane Jose, CA( California) በመሆኑ ይህንኑ አውቃችሁ ወደዚያው እንድትጓዙ፣*
2. *በሚኒሶታ ለማካሔድ ያሰባው የወያኔ ከፋፋይ ክንፍ ስለሆነ ወደ ቦታው የሚኒሶታ ሕዝብ እንዳይሄድ፣*
3. *ይህን የወያኔን  ከፋፋይ ቡድን የሚኒሶታ ኢትዮጵያዊ በነቂስ  ወጥቶ ተቃውሞ እንዲያካሄድ፣*
4. *ለወያኔ የሚያገለግሉ አሰልጣኞች ልጆቻችሁን ኣታለው ኢትዮጵያዊ የሆነ ስፖርት ዝግጅት አስመስለው ለመጠቀም እየተራወጡ ስለሆነ ወላጆች ልጆቻችሁን ስለሁኔታው በማስረዳት ከነዚያ አሰልጣኖችና ቡድኖች እንድርቁ እንድታደርጉ፣ ለመስጣት የተዘጋጀው ገንዘብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተዘረፈና የደም ገንዘብ መሆኑን እንዲታስረዱ፣*
5. *ESFNAONE ብሎ እራሱን የሰየመው ቡድን ካንድ ዘር የተወጣጣና ፍርፋሪ ለቃሚ በሆኑ ሆዳም ሐብታሞች የተሰበሰቡበት የወያኔ ከፋፈዮች ጎረኖ በመሆኑ እስፖርት ለማካሔድ ሳይሆን ዓላማው በእስፖርት ስም ፖለቲካ መስራትና ሕዝብን መከፋፈል ስለሆነ፤ የሚኒሶታ ሕዝብ እርስ በርስ በማነጋገር እንደዋሽግንተኑ ሕዝብ ባዶ እስታድየም ይዘው እንዲቀሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ ሁላችንም ግዴታችንን እንወጣ። ወያኔና ተላጣፊዎቻቸው ኢትዮጵያን ለማጥፋት ስሰሩ እንጂ ሲያለሙ ኣይታወቁም ።የኢትዮጵያ እስፖርት ስላሉ መታለል የለብንም።*

*በሚኒሶታ የተደራጀው የተቃውሞ ግብረ ኃይል*